# እውነቱ ይነገረን

ኢብሳ ነሜራ 10-03-17

ለዘመናት በጉርብትና የኖሩት የኦሮሞና የኢትዮጵያ ሶማሌ ህዝቦች ግንኙነት ድንገት ያለአሟሉ ካልሻከርኩ እያለ ነው። በስተደቡብ ምስራቅ ኦሮሚያ ጉጂና ቦረና ዞኖች፣ በስተምስራቅ ምዕራብና ምስራቅ ሃረርጌ ዞኖች በሺህ ኪሎሜትሮች የሚለካ ወሰን ላይ የሚኖሩ በሚሊየን የሚቆጠሩ ኦሮሞዎች ከኢትዮጵያ ሶማሌዎች ጋር ድንበር ይጋራሉ። ሁለቱ ህዝቦች ድንበር ብቻ አይደለም የሚጋሩት፤ ባህልም ተጋርተዋል፣ ተዋልደው በደም ተዋህደዋል። አብኞቹ በተዋሳኝ ድንበር ላይ የሚገኙ ኦሮሞዎችና ሶማሌዎች አንዱ የሌላውን ቋንቋ አቀላጥፈው ይናገራሉ። አርብቶ አደርነትንም ይጋራሉ። ባለፉት ሥርአቶች ሲደርስባቸው የነበረውን ተመሳሳይ የብሄራዊ ጭቆና ታሪክም ይጋራሉ።

ሁለቱ ተዋሳኝ ብሄሮች በአማዛኙ አርብቶ አደር በመሆናቸው አልፎ አልፎ በግጦሽ ሳርና በውሃ ሽሚያ ግጭት ወስጥ የሚገቡባቸው አጋጣሚዎች መኖራቸው ባይካድም፣ የመንግስት ጣልቃ ገብነት ሳያስፈልጋቸው በራሳቸው ባህላዊ የሽምግልናና የእርቅ ሥርአት እየፈቱ አብሮነታቸውንና ሰላማቸውን አጽንተው መዝለቅ ችለዋል። አሁን ይህ የዘመናት አብሮነት ከዚህ ቀደም ታይቶ የማይታወቅ ፈተና እንደገጠመው እየሰማን ነው።

እነዚህ የኦሮሞና የኢትዮጵያ ሶማሌ ተወሳኖ ህዝቦች አንዱ ሌላው ላይ ተነስቶ ሜንጫ ማስንዘሩን፣ ክላሽንኮቭ መተኮሱን የሚያጋግጥ ተጨባጭ አስረጂ ባይኖርም *በሁለቱ ብሄሮች መሃከል ግጭት ተቀስቅሷል* እየተባለ ነው። *ከድንበር ማዶ የሚኖሩት የኢትዮጵያ ሶማሌ ብሄር ተወላጆች ተከበው ገደሉን የሚሉ* የኦሮሞ ብሄር ተወላጆች አላጋጠሙኝም። ይሁን እንጂ በሁለቱም በኩል የሞቱና የተፈናቀሉ አሉ፤ በታጣቂዎች በተተኮሰ ጥይት ህይወታቸውን ያጡ፥ ተሳድደው መኖሪያቸውን ለቀው የተፈናቀሉ ሰዎች። ነገሩ ግራ አጋቢ ነው።

አሁን በሁለቱ ክልሎች ወስጥና መሃከል ለተፈጠረው የሰላም መደፍረስና የሰላም መደፍረሱ ላስከተለው የሚፈናቀል ቀወስ መፍትሄ ለማበጀት በፌደራል መንግስት ደረጃ አንድ ኮሚቴ ተደራጅቷል፤ በፌደራል ጉዳዮችና በአርብቶ አደር አካባቢዎች ልማት ሚኒስቴር የሚመራ ኮሚቴ። ይህ ኮሚቴ የብሄራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን፣ የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽህፈት ቤት፣ የጸጥታ አካላትና የኢኮኖሚ ልማት ማስሪያ ቤቶች የተካተቱበት ነው።

በሁለቱ ክልሎች አዋሳኝ አካባቢዎች ግጭት መቀስቀሱን፣ በዚህም ከአዋሳኝ አካባቢዎች ውጭ በሆኑ አካባቢዎች የሚኖሩ ሰዎች ላይ ጭምር ጥቃት ማስንዘሩንና ከመኖሪያቸው እንዲፈናቀሉ መደረጉን ተከትሎ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር መግለጫ ሰጥተዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚህ መግለጫቸው፣ ግጭት

የተቀሰቀሰባቸውን የሁለቱ ክልሎች አካባቢዎች የሰላም ሁኔታ ወደነበረበት ለመመለስ ዋና ዋና መንገዶች በመከላከያና በፌደራል ፖሊስ ሃይል ጥበቃ ሥር እንዲሆኑ፣ እንዲሁም የፌደራል የጸጥታ ሃይሉ የሰው ሕይወት በማጥፋትና አካላዊ ጉዳት በማድረስ የሚጠረጠሩ ሰዎችን በቁጥጥር ሥር አውለው ለፍርድ እንዲቀርቡ እንዲያደርጉ ትዕዛዝ መተላለፉን አስታውቀዋል። በሁለቱ ክልሎች መካከል የሰብዓዊ መብት በመጣስ የሰው ሕይወት ያጠፉ የፀጥታ ኃይል አባላትም ይሁኑ ሌሎች አካላት ህግ በሚያዘው መሰረት እርምጃ እንዲወሰድባቸው እንደሚደረግም አስታውቀዋል። ግጭቱ በተከሰተባቸው አካባቢዎች የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የሰብአዊ ማብት ጥሰትን እንደሚያጣራም አስታውቀዋል።

የአካቢውን ሰላም የማስከበር ሃላፊነት የተጣለበት የደቡብ ምስራቅ እዝ ሰሞኑን እንዳስታወቀው አሁን ግጭት ተቀስቅሶ በነበረባቸው የሁለቱ ክልሎች አዋሳኝ አካባቢዎች ሰላም ሰፍኗል። በግጭቱ ወስጥ መሳተፋቸው በማስረጃ የተረጋገጠባቸው ግለሰቦችን በቁጥጥር ስር የማዋል ስራም እየተከናወነ ነው።

ከወሰን ጋር ተያይዞ በተፈጠረው ግጭት ሳቢያ በዜጎች ላይ የተፈፀመና የሚፈፀሙ የመብት ጥሰቶችን ለሚፈተሽ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን አጣሪ ቡድን መላኩም ታውቋል። የሰብአዊ መብት ሁኔታ አጣሪ ቡድኑ ምርመራውን አጠናቆ እንዳበቃ የችግሩን ስፋትና ምክንያት ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል።

በሌላ በኩል ለተፈናቃዮች የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ እየተደረገ ነው። በተለይ በኦሮሚያ ክልል ከ50 ሺህ በላይ ለሆኑት ከኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል ለተፈናቀሉ ዜጎች የእርዳታና መልሶ ማቋቋሚያ ህዝባዊ ንቅናቄ ተፈጥሯል። ይህ ህዝቡ ወገኖቹን ለመርዳት ከዳር እስከዳር ያሳየው መነቃቃት በስነልቦና ተጎድተው የነበሩትን ተፈናቃዮች ተስፋ አለምልሟል።

እንግዲህ፣ በሁለቱ ክልሎች መሃከል የተፈጠረው ግጭት መንስኤ ወሰን እንደሆነ ነው የሚነገረው። ይሁን እንጂ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ግጭቱ አዋሳኝ አካባቢ በሚኖሩ የሁለቱ ብሄሮች መሃከል የተፈጠረ አለመሆኑ፣ በሌላ በኩል ጥቃቱ በአካባቢው ነዋሪነት በሚይታወቁ በተደራጁ ከፍተኛ የጦር መሳሪያ በታጠቁ፣ በሰለጡኑ ሰዎች የተፈጸመ መሆኑ የግጭቱ መንስኤ የወሰን አለመግባባት የመሆኑን ነገር ጥያቄ ላይ ይጥለዋል። በሁለቱ ክልሎች አዋሳኝ አካባቢዎች ከአስራ ሶስት ዓመታት በፊት ከወሰን ጋር በተያያዘ ማጠነኛ ግጭቶች ተቀስቅሰው ጉዳዩ በህዝበ ወሳኔ እልባት ተበጅቶለት እንደነበረ ይታወሳል። ይህ በህዝበ ወሳኔ የተረጋገጠው ወሰን በሜዳ ላይ ሳይካለል መቅረቱ እንደመንግስት ችግር የሚወደሰድ ቢሆንም፣ አለመካለሉ በራሱ በዚህ ደረጃ ግጭት ሊቀሰቅስ ይችላል ተብሎ አይገመትም።

ወሰን ሜዳ ላይ አለመካለሉ ትናንሽ መንደሮችና ጎጆዎች ወደየትኛው ክልል እንደሆኑ ማለየት ያስቸግር እንደሆን እንጂ ቀበሌዎች ወደየትኛው ክልል እንደሚገኙ ጥያቄ አያስነሳም። በመሆኑም ግጭቱ በምንም አግባብ ወሰንን መነሻ ያደረገ የህዝቦች ግጭት ነው ብሎ መውሰድ አይቻልም። እናም ግጭቱ ለምን ዓላማ በማን እንደተቀሰቀሰ ተጣርቶ ለህዝብ ይፋ ሜደረግ አለበት። በዚህ ላይ የሚደረግ ሚድበስበስ ግጭቱን

በማጻፈን ወቅት እየጠበቀ እንዲያያዝ ከማድረግ ያለፈ የሚያስገኘው ጥቅም እንደሌለ ማታወቅ አለበት። እውነተኛው የችግሩ ምንጭና ፈጻሚ ካልታወቀ ዘላቂ መፍትሄ ለማበጀት የሚደረገው እንቅስቃሴ የይስሙላ ነው የሚሆነው። ወይም ግቡን ሳይመታ የሚቋጭ የአንድ ሰሞን ወሬ ከመሆን አይዘልም።

ለችግሩ ዘላቂ መፍትሄ አለማበጀት በሁለቱ ህዝቦች ማካከል የተፈጠረውን በጥርጣሬ ወደመተያየት እያመራ ያለ መድናገር ያባብሰዋል። ይህ ደግሞ በችግሩ ሳቢያ የተፈናቀሉ ዜጎችን አሁን እንደሚወራው ወደነበሩበት የመመለሱን ተግባር የሚይቻል ያደርገዋል። የተፈናቀሉትን ሰዎች ወደነበሩበት መመለስ ዳግም ተመሳሳይ ችግር እንደሚይፈጠር ዋስትና ሚረጋገጥን ይሻል። አሁን የምንመለከተው በሁለቱ ህዝቦች ማካከል የሚታይ አንዱ ሌላውን በጥርጣሬ የመመልከት አዝማሚያ ካልተወገደ አንዱ ህዝብ በሌላው ክልል በሰላም የመኖር ዋስትና ሊያገኝ አይችልም። እናም እውነቱ ፍርጥ ብሎ መውጣት አለበት። እውነቱ የሚመር እንኳን ቢሆን፣ የሚመር መድሃኒት ያድናል እንዲሉ፣ በማንኛውም ጊዜ የሚያመረቅዝ በሽታ ይዞ ከመኖር መራራውን እውነት ተጎንጭቶ መዳን ነው የሚሻለው። እውነቱ እስካልወጣ ደረስ መሬት ላይ ወሰን ማካለል በራሱ ዘላቂ መፍትሄ እንደማያመጣም ማታወቅ አለበት።

በኦሮሚያና በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልሎች ማካከል የተፈጠረው ግጭት በአጠቃላይ የሃገሪቱን ፖለቲካ ወደአለመረጋጋት ወስጥ ሊከት እንደሚችልም ማታሰብ አለበት። ሰሞኑን እንደምንመለከተው የአሃዳዊ ሥርአት ተስፈኞች ከተቀበሩበት አፈራቸውን እያራገፉ እየተነሱ ነው። እትግጥ ኢትዮጵያ ካሁን በኋላ ወደአሃዳዊ ሥርአት ልትመለስ አትችልም። አሃዳዊ ሥርአትን የመመለስ ጉዳይ ከህልም የተለየ አይደለም። ካሁን በኋላ ለብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ዕወቅና የነፈገ ማንኛውንም አይነት የመንግስት ሥርአት መመስረት የሚያስችል ነባራዊ ሁኔታም የለም። በመሆኑም የአሃዳዊ ስርአት ተስፈኞች ህይወት የመዝራት አቅም ባይኖራቸውም፣ የብሄሮች ግጭት ገጽታ ያላቸው ሁኔታዎች እስካሉ ደረስ በተለይ በከተሞች አካባቢ ወሻንብር መፍጠር የሚያስችላቸው እድል ሊያገኙ መቻላቸው እውነት ነው። ይህ ደግሞ ለሁከትና ግርግር በር ይከፍታል። ማታኑ የአሃዳዊ ፅርአት ተስፈኞች ወደመቃብራቸው እንዲመለሱ ለማድረግ ችግሩ ከፌደራላዊ ስርአቱ ያልመነጨ መሆኑን በግልጽ በሚያሳይ ሁኔታ በችግሩ ዙሪያ ያለው እውነት ፈርጦ መውጣት አለበት።

በሌላ በኩል ግጭቱ የተመራው የፌደራል መንግስት ነው የሚሉ በህዝብ ዘንድ የመደመጥ እድል እያገኙ የመጡ ድምጾች መኖራቸውን ማስተዋልም ተገቢ ነው። የፌደራል መንግስቱ የኦሮሞን ህዝብ ለማጥቃት፤ ኢህአዴግ ወስጥ እየጎለበተ አልታዘዝ እያለ መጣ ያሉትን የኦሮሞ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦህዴድ) ለማዳከም ያደረገው ነው፤ ጥቃቱን የፈጸመው ሃይል በፌደራል መንግስት ብቻ የሚታዘዝ አካል ነው የሚለው ወሬ ተሰሚነት እያገኘ ማምጣቱን ማስተዋል ብልህነት ነው። ይህ ወሻንብር እውነቱ ካልወጣ በስተቀር ጉልበት የማግኘት እድል ይኖረዋል። እናም እውነቱ ሳይሸሸግና ሳይድበሰበስ መውጣት አለበት።በአጠቃላይ፤ በኦሮሚያና በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልሎች ማካከል የተፈጠረው ግጭት ዘላቂ መፍትሄ ሊበጅለት ይገባል። ዘላቂ

መፍትሄ የማበጀቱ ጉዳይ ግን የችግሩ ምንጭና ግጭቱን የሚሩ ግለሰቦችና ቡድኖች ማንነት ምንም ሳይድበሰበስና ሚዛናዊ ለመሆን በሚል ስሌት ተቀንሶና ተጨምሮ ሳይደበዝዝ ይፋ እንዲወጣ ይሻል።